የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን
Ethiopian Agricultural Authority

# ዜና መጽሔት

በሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈፃሚ በየ2 ወሩ የሚወጣ የውስጥ ጋዜጣ

ቅጽ 1 ቁጥር 66 — መስከረም 2017ዓ.ም

ርዕይ

በዓለምአቀፍ ደረጃ ዕውቅናና ተቀባይነት ያለው የግብርና ተቆጣጣሪ ተቋም ሆኖ ማየት፤

ተልዕኮ

የግብርና ቴክኖሎጂን፣ አገልግሎቶችን፤ ግብዓቶችና ምርቶችን ጥራት፣ ደህንነት፣ ፍቱንነት፣ፈዋሽነት፣ጤናማነትና ቀልጣፋነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል፤ መልካም ስም ያለውን፣ለአካባቢ ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ የቁጥጥር ተቋምና ስርዓት በመገንባትና የግብርና ቁጥጥር ስራዎችን በመተግበር፣ የሀገር ውስጥ እና የአለም ገበያ ተደራሽነትና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ለላቀ ሀገራዊ ጥቅምና የኤኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቀትን አስተዋፅኦ ማበርከት

እሴቶች

- ታማኝነት
- ሚስጥር ጠባቂነት
- ቁርጠኝነት
- የህግ የበላይነት
- ተጠያቂነት
- ለደንበኛና ተገልጋይ ትኩረት
- አለማዳላት
- አጋርነት
- ግልጽነት።
- ምላሽ ሰጪነት

አድራሻ፡- ፖ.ሳ.ቁ 31303
ስልክ ቁጥር ፡- 0115534520
የውስጥ መስመር፡- 227/234
የፌስቡክ ገጻችን፡- Ethiopian Agri cultural Authority
የቴሌግራም ገጻችን፡- eaa_123
ዌብሳይት፡- www.eaa.gov.et

## በዘር ጥራት ቁጥጥር ረቂቅ መመሪያዎች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደረገ።









በኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የእፅዋት ዘርና ዝርያ ጥራት ቁጥጥር መሪ ስራ አስፈፃሚ ባዘጋጃቸው በዘር ጥራት ቁጥጥር ረቂቅ መመሪያዎች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በአዳማ ከተማ ውይይት ተደረገ።

የውይይት መድረኩን በንግግር የከፈቱት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ክቡር አምባሳደር ድሪባ ኩማ እንኳን ደህና መጣችሁ ካሉ በኋላ የዘር ጥራት ቁጥጥሩን ውጤታማ ለማድረግ በተዘጋጁ ረቂቅ መመሪያዎች ላይ አስተያየት ለመውሰድ፤ መመሪያዎችን ለማሻሻልና የበለጠ ለማጥራት ከዚያ በኋላም የጋራ ግንዛቤ ይዘን በህግ ማዕቀፍ ስራችንን እንድንመራ ለማድረግ የሚጠቅመን ስለሆነ ከዚህ መድረክ ሰፊ ግብዓት እንጠብቃለን ብለዋል።

በመቀጠልም የእፅዋት ዘር ብዜት እና ንግድ ስራ የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና አስተዳደር ረቂቅ መመሪያ፤ የዘር ጥራት ደረጃ ስለማያሟላ የእዕዋት ዘር አጠቃቀምና አወጋገድ ረቂቅ መመሪያ፤ ጥራቱ የተገለፀ ዘር ማስፈፀሚያ ረቂቅ መመሪያ እና ለራስ አገዝና ሶስተኛ ወገን ዘር ጥራት ማረጋገጥ ፈቃድ አሰጣጥና

**ወደ ገጽ 2 ዞራል!**

**ከገጽ 1 የዞረ..**

አስተዳደር ረቂቅ መመሪያ ላይ በተለያዩ ባለሙያዎች በቅደም ተከተል ከሰፊ ማብራሪያ ጋር እንዲቀርብ ተደርጓል። በመጨረሻም በእያንዳንዱ ረቂቅ መመሪያ ላይ አሉን የሚሉትን አስተያየት እና የግልፅነት ጥያቄዎች እንዲያቀርቡ ከተደረገ በኋላ ማብራሪያ ያስፈልጋቸዋል ለተባሉት ሀሳቦች በሚመለከታቸው አካላት ማብራሪያ በመስጠት ሌሎች ሃሳቦችን ደግሞ እንደ ግብዓት እንደሚጠቀሙባቸው የጋራ መግባባት ላይ ተደርሶ ውይይቱ ተጠናቋል።



**በእንስሳት መድሃኒት አስመጪ ድርጅት ውስጥ ላሉ የቴክኒክ ሃላፊዎች በ E- Service አጠቃቀም ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጠ።**

በእንስሳት መድሃኒት አስመጪ ድርጅት ውስጥ ላሉ የኢ ሰርቪስ አገልግሎቱን ለሚጠቀሙ 60 የቴክኒክ ሃላፊዎች በ E-Service አጠቃቀም ላይ በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት አዳራሽ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጠ። ስልጠናውን በንግግር የከፈቱት በኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የእንስሳት መድኃኒት ሬጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ የሆኑት ዶ/ር ሰለሞን ከበደ ሲሆኑ እሳቸውም ከዚህ በፊት የእንስሳት መድኃኒት አስመጪና ላኪ ድርጅቶች ለአራት አመታት የወጪና የገቢ ንግድ አገልግሎት ያገኙ የነበረው በአንድ መስኮት እንደነበር ገልፀው ከዚህ በተጨማሪ የእንስሳት መድኃኒት ምዝገባ አገልግሎቱን ለማዘመን ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የአምስት አገልግሎቶችን የስራ ፍሰት (Work flow): የማመልከቻ ቅፅ እና አስፈላጊ ሰነዶች ለተለያዩ አገልግሎቶች በሲስተሙ ላይ የማስገባት ስራ በማጠናቀቅ አገልግሎቱን የሚሰጡ የእንስሳት መድኃኒት ምዝገባ ባለሙያዎች ስልጠና እንዲወስዱና ልምምድም እንዲያደርጉ የተደረገ መሆኑን አስታውሰዋል።

አያይዘውም ይህ ዛሬ የሚሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በእንስሳት መድሃኒት አስመጪ ድርጅት ውስጥ ላሉ የኢ-ሰርቪስ አገልግሎቱን ለሚጠቀሙ የቴክኒክ ሃላፊዎች በሶስት አገልግሎቶች ማለትም New Veterinary pharmaceutical registration፣ Veterinary drug re registration  እና Veterinary drug variation registration በተሰኙ አገልግሎቶች የ E- Service አጠቃቀም ላይ የተሻለ ግንዛቤ ፈጥረው ስራዎቻቸውን እንግልትን የሚታደግና ጊዜ ቆጣቢ የሆነውን የዘመነ ቴክኖሎጂን ተጠቅመው ፈጣን አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ ለማገዝ ነው ብለዋል ::

ይህን አሰራር በቴክኖሎጂ የማዘመን ስራ በዚህ ብቻ የሚያበቃ ሳይሆን በቀጣይም ሁለት አገልግሎቶችን (New Veterinary biological registration እና Veterinary medical devise registration ስራ ለማስጀመር በዝግጅት ላይ እንዳሉ ገልፀዋል።

PAGE 3

## “የሚሌ የእንስሳት ኳራንቲን ለሌሎች ሀገራት የልምድ መቅሰሚያ ሆኗል” - ግርማ አመንቴ (ዶ/ር)



(ሰመራ፣ ነሐሴ 25 ቀን 2016 ዓ.ም፣ ግብርና ሚኒስቴር)

የግብርና ቤተሰብ የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ተግባር ማስጀመሪያ መርሀ ግብር ከተጠናቀቀ በኋላ ውጤታማ እየሆነ ያለው የሚሌ የእንስሳት ኳራንቲን (የቁም እንስሳት ማቆያ ማዕከል) ተጎብኝተዋል፡፡

በጉብኙቱ ወቅት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አወል አርባ የሚሌ የእንስሳት ኳራንቲን ክልሉ ያለውን ትልቅ ሀብት ወደ ዶላር የቀየረ ፕሮጀክት መሆኑን ጠቅሰው ለላቀ ውጤት ከግብርና ሚኒስቴር ጋር ቅንጅታዊ ስራ አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ገልፀዋል፡፡

የክልሉን አርብቶ አደሮች በማደራጀትም ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እናደርጋለን ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፣ የሚሌ የእንስሳት ኳራንቲንን ለውጤት ያበቁትን አካላት ሁሉ አመስግነዋል፡፡

የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) የሚሌ የቁም እንስሳት ማቆያ ማዕከል በቅርብ ጊዜ ግንባታው ተጠናቅቆ ስራ ቢጀምርም በአጭር ጊዜ ውስጥ ስኬታማ ስለሆነ ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ከማዕከሉ ልምድ መውሰድ ጀምረዋል ብለዋል፡፡

አፋር ክልል አርብቶ አደሮች ባላቸው የእንስሳት ቁጥር ልክ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በክልሉ የተጀመረው የእንስሳት መኖ ልማትም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ሚኒስትሩ ተናግረዋል፡፡ ማዕከሉ ዓለም አቀፍ ደረጃውን ጠብቆ የተገነባ ሲሆን በአንድ ጊዜ ከ400 ሺህ በላይ የቁም እንስሳትን የማቆየት አቅም አለው፡፡ የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አምባሳደር ድሪባ ኩማ ማዕከሉ ዓለም አቀፍ ደረጃውን በማሟላት ዛሬ በኢትዮጵያ ሰርተፊኬት የቁም እንስሳት ወደ ውጭ እንደሚላኩ ገልፀዋል፡፡

በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ስራ የጀመረው የሚሌ የእንስሳት ኳራንቲን በበጀት ዓመቱ 256 ሺህ የቁም እንስሳትን ወደ ተለያዩ ሀገራት በመላክ 18 ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን ጠቅሰው ይህ መልካም ተሞክሮ ወደ ሌሎችም ይስፋፋል ብለዋል፡፡

# የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በ2017 በጀት ዓመት እቅድ ላይ ውይይት አደረገ፡፡



የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን አመራሮች በተገኙበት በ2017 በጀት ዓመት እቅድ ላይ በአዳማ ከተማ ኤፍታህ ሆቴል ውይይት አደረገ፡፡


የእቅድ ውይይቱን መድረክ በንግግር የከፈቱት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ክቡር አምባሳደር ድሪባ ኩማ ሲሆኑ እሳቸውም አገራችን ኢትዮጵያ አዲስ ዘመን በመጣ ቁጥር አዳዲስ ሀሳቦችን የማመንጨት የማቀድ ካለፈው ዓመት ስህተቶችና ስኬቶች የመማርና በቀጣይ የተሻለ የመፈፀም በይቅርታና መልካም ምኞት ለመሻገር ይመኛሉ ያቅዳሉ በተለይ የጳጉሜ ወርን እንደ 13ኛ ወር በመቁጠር ለ5ቱ ቀናት የተለያየ ስያሜ ተሰጥቷቸው ከዛሬ ጳጉሜ 1 ጀምሮ በተለያዩ መሪ ቃሎች እንደሚከበርና የዛሬዋ ቀንም የመሻገር ቀን ተብሎ እንደሚጠራ በመግለፅ ከወቅታዊ የሀገራችን ችግር አኳያ ደግሞ ወደ ሚጨበጥ ተስፋ የምንሻገርበት ነው በማለት እንኳን አደረሳችሁ ብለዋል፡፡ አያይዘውም የተቋማችን የ2017 በጀት ዓመት እቅድ ለማዘጋጀት መነሻዎቹ እናንተ ብትሆኑም ተቋሙ ከተጣለበት ሀገራዊ ሀላፊነት አኳያ ተቃኝቶ ግቦቹ የተቀመጡ እንደሆነና ለእያንዳንዶቹ ግቦቹም የሚጠበቅ ውጤት የተቀመጠለት በመሆኑ ተቋማችን አሁን ካለበት ወደ ተሻለ ደረጃ የሚያሻግሩ በመሆኑ በእቅዱ ላይ በሰፊው በመወያየትና የጋራ በማድረግ እንዲሁም እቅድ እስከ ፈፃሚዎች ድረስ ወርዶ ለእቅዱ ተግባራዊነት ሁሉም ሊረባረብ እንደሚገባ አፅንኦት ሰጥተው ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ተቋማችንን ውጤታማ ለማድረግ ሁላችንም ትኩረት ልናደርግ የሚገቡን ነገሮች ካስቀመጥነው ራዕይና ተልዕኮ በመነሳት ምን ማሳካት እንዳለብን ደጋግሞ ማሰብ እንደሚያስፈልግ፤ የምንሰራበትን ውስጣዊና ውጫዊ አካባቢን በደንብ መገንዘብና መረዳት፤ ተቋሙ ከሌላው ተቋም ወይም አካላት ጋር ያለውን ትስስር በተለይ ከኮሙኒኬሽን አኳያ በደንብ መስራት እንዲሁም ሁልጊዜ አዳዲስ ነገሮችን ለመፍጠር መጣር እንደሚያስፈልግ በሰፊው አብራርተዋል፡፡

በመቀጠልም የስትራቴጅክ ጉዳዮች ስራ አስፈፃሚ ወ/ሮ መሰረት አበባው የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድን ያቀረቡ ሲሆን በቀረቡት ዕቅዶች ላይ የተለያዩ ሀሳቦችና አስተያየቶች ተነስተዋል፡፡ በመጨረሻም ለተነሱ ጥያቄዎች ማብራሪያ ከተሰጠ በኋላ ሁሉም አመራርና ሰራተኛ በእቅዱ ላይ ግልፅነትን ፈጥሮ ለለውጥ ከተነሳ በእያንዳንዱ ግቦች ላይ የተቀመጡ ውጤቶችን ማሳካት ስለሚቻል ስራችንን ስናከናውን የሀገራችንን ህዝብ ጤና ከመጠበቅና ሀገራችን በአለማቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላት ሀገር እንድትሆን አልሞ መስራት እንደሚያስፈልግ ለዚህ ደግሞ ከሌብነትና ከደላላ በፀዳ መልኩ ስራችንን ማከናወን እንዳለብን የጋራ መግባባት ላይ ተደርሶ የውይይት መድረኩ ተጠናቋል፡፡

## የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የስራ ሀላፊዎችና ሰራተኞች የደም ልገሳ ፕሮግራም አካሄዱ፡፡





የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች "በደም እጦት ምክንያት የምትሞት እናት እንዲሁም ዜጋ እንዳይኖር የዜግነት ግደታችንን እንወጣ" በሚል መሪ ቃል የደም ልገሳ ፕሮገራም አካሄዱ፡፡

የደም ልገሳ ፕሮግራሙ እንዲሳካ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች አካቶ ትግበራ ስራ አስፈጻሚ እና የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈጻሚ በጋራ በመሆን አስተባብረዋል፡፡

በበጎ ፈቃድ የደም ልገሳ ፕሮግራሙ ላይ ደም በመለገስ ከተሳተፉት ደም ለጋሾች መካከል የባለስልጣኑ የመሰረታዊ አገልግሎት ስራ አስፈጻሚ አቶ እርቅሁን ሙላቱ አንዱ ሲሆን ደም ለሚያስፈልገው ወገናቸው ደም ሲለግሱ ለ4ኛ ጊዜ መሆኑን ገልፀው ደም በመለገስ የሌላን ህይወት መታደግ በጎ ተግባርና ደስታን የሚፈጥር ነው ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል የእቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማ ቡድን መሪ የሆኑት ወ/ሮ አበራሽ ገደቡ በደም ልገሳ ፕሮግራሙ ላይ ደም በመለገስ በቀዳሚነት የተሳተፉ ሲሆን ደም በመለገስ የማይተካውን እና ክቡር የሆነው የሰው ልጅ ህይወት መታደግ ትልቅ የበጎነት ተግባር በመሆኑና በዚህ የደም ልገሳ ፕሮግራም ላይ በመሳተፋቸው ደስታኛ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ወ/ሮ አበራሽ አክለውም ደም በመለገስ ሰውነታችን አዳዲስ ሴሎችን በማምረት ጥሩ የጤና መሰረት እንዲኖረንና ሌሎች የጤና ጥቅሞችን እንድናገኝ ያደርገናል እንጂ የሚጎዳን ተግባር ባለመሆኑ ሁሉም ሰው በበጎ ፈቃድ ላይ ተመስርቶ ደም በመለገስ የወገኑን ህይወት መታደግ አለበት ብለዋል፡፡

በመጨረሻም የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች አካቶ ትግበራ ስራ አስፈጻሚ የሆኑት ወ/ሮ ትዕግስት ወ/አገኘሁ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አንዱ የመረዳዳት ባህላችን መገለጫ ሲሆን ደም በመለገስ ደም ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች መድረስ ትልቅ በጎነት እንደሆነ ገልጸው በተዘጋጀው የደም ልገሳ ፕሮግራም ላይ በፈቃደኝነት ደማቸውን የለገሱ የባለስልጣኑን አመራሮችና ሰራተኞችን አመሰግነው በቀጣይም ይህ በጎ ተግባር በዚህ የሚቆም ሳይሆን ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሁሉም በፈቃደኝነት በመሳተፍና ሌሎችን በማስተባበር ደም የሚያስፈለገው ወገኑን ህይወት መታደግ አለበት በማለት አሳስበዋል፡፡

**የዕፅዋት ሪጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ በ2017 በጀት ዓመት በዕቅዶቹ ላይ ትኩረት አድርጎ እንደሚሰራ አስታወቀ**

በ 2017 በጀት አመት በስራ ክፍሉ በዕቅድ ከተያዙ ቁልፍና ዋና ዋና ተግባራት መካከል ወደ ወጪ የሚላኩና የሚገቡ የዕፅዋትና የዕፅዋት ውጤቶች ፍቱንነታቸው፣ ውጤታማነታቸው ፣ ጥራታቸው እና ደህንነታቸው የተረጋገጠ እንዲሆን ማስቻልና በተጨማሪም አምራችነት፣ አስመጪነት፣በላኪነት፣ በማዕጠንት /fumigators/ ፣አከፋፋይነት በምርምር ማዕከላት ወዘተ ድርጅቶች እና ተቋማት የመመዝገብ እና የመቆጣጠር ስራ ማካሄድ።

በ2017 በጀት ዓመት ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የሚላክ የዕጽዋትና የዕፅዋት ዉጤቶች በተመለከተ 87531 ሜትሪክ ቶን የሚሆን የዕፅዋት ዉጤቶች ጤንነቱ፣ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ እንደሚላክ የተገለፀ ሲሆን። ከዚህ ጋር ተያይዞ ለውጭ ገበያ በሚቀርቡ በተመረጡ 300 የግብርና ምርቶች ላይ የማዕጠንት/Fumigation/ክትትል ማድረግ፣ ወደ ውጪ ለሚወጣ 50,000 የዕፅዋት ምርት የጤንነት ማረጋገጫ ሠርተፍኬት መስጠት፣ወደ ውጭ የሚላኩ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች ተቀባይነታቸውን የማሳደግ እና የተቀባይ ሃገራትን ቅሬታ(Notification) የመቀነስ ስራዎች ማከናወን፣ለ56 የአበባ፣የአትክልትና ፍራፍሬ እርሻዎችን በየሩብ ዓመቱ የመስክ ቁጥጥርና ክትትል የማድረግና ሞያዊ ድጋፍ የመስጠት ስራ ማከናወን፣ ወደ አውሮፓ ህብረት የሚላኩ የሮዝ አበባ ምርቶችን 8 ጊዜ ውጫዊ ኦዲት ማድረግ፣ ለ44 የአበባ፣የአትክልትና ፍራፍሬ እርሻዎችን በየሩብ ዓመቱ የመስክ ቁጥጥርና ክትትል የማድረግና ሞያዊ ድጋፍ የመስጠት ስራ ማከናወን፣ Xylella fastidiosa ጨምሮ ሌሎች የተቀባይ ሀገራትን መስፈርት ቅኝት በማካሄድ እንዲሁም በላብራቶሪ እንዲመረመር በማድረግ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የመላክ ስራ ማከናወን፣ለዕፅዋትና ዕፅዋት ዉጤቶች ተቀባይ ሀገር የተባይ ስጋት ትንተና ቴክኒካል መረጃ/ሰነድ የመላክ ስራ ማከናወን፣ ለጥራጥሬ እና ቅባት እህሎች አበጣሪ እና አቀነባባሪ እና ለቡና አበጣሪ እና ላኪ ድርጅቶች በምግብ ደህንነት አስተዳደር ስርዓት ላይ : ብሄራዊ እና አለምአቀፍ ደረጃዎች ላይ 4 ጊዜ ስልጠና እና የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት፣ የሰሊጥ አምራቾች በሳልሞኔላ ምክንያት ወደ አውሮፓ ኤክስፖርት መቀዛቀዝ እንዳይከሰት ተገቢ የሆነ የላብራቶሪ ምርመራ እንዲያካሂዱ የመከታተል ስራ መስራት፣ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በምግብ ደህንነት አስተዳደር ስርዓት ላይ፤ብሔራዊ የመከታተያ ሥርዓት (National traceability system) ወርክ ሾፕ ማካሄድ፣ በእፅዋት ምርት ጥራትና ደህንነት ከእርሻ እስከ ገበታ ለክልልና ከተማ አስተዳደር ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች ስልጠና እንደሚሰጥ ተገልጿል።

ጤንነቱ፣ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች በዚህ ዓመት 60000 ሜትሪክ ቶን የሚሆን የዕጽዋት ውጤቶች የጤንነትና ጥራት ማረጋገጫ ስራዎች እንደሚከናወኑ የተገለፀ ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞም የዕፅዋት ኳራንቲን ተባይ ወደ ሀገሪቱ ከመግባቱ በፊት መተንበይና ገብቶ ሲገኝ በአፋጣኝ የመቆጣጠሪያ ዘዴ በመጠቀም ተባዩ በአስቸኳይ እንዲጠፋ ክትትል ማድረግ፣ ወደ አገር ውስጥ

PAGE 7

በሚገቡ 2024 ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ዉጤቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች የሚገቡባቸውን መስፈርቶች ማሟላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ የጉምሩክ ማስለቀቂያ ደብዳቤ መስጠት በድህረ መግባት ኳራንቲን (Post Entry Quarantine) ማለፍ ያለባቸውን እፅዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች 6 ጊዜ ክትትል ማድረግ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ 2,195 ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤቶችና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ መስጠትና ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ዕፅዋትና የዕፅዋት ዉጤቶች የተባይ ስጋት ትንተና የመስክ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ እንዲሁም ለዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች የጥራት እና ደህንነት የደረጃዎች ዝግጅት እንደሚካሄድ በዕቅድ ተይዟል፡፡

ሌላው በ2017 ዓ.ም 230 ለሚደርሱ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም የዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤት ወደ ውጪ ሀገር ለመላክና ለማስመጣት እንዲሁም በማጥንት ሰራ ላይ ለተሰማሩ 200 አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች/ግለሰቦች አስፈላጊውን የቢሮና የመጋዘን ኢንስፔክሽን በማካሄድ የብቃት ማረጋገጫ እንደሚሰጥ ተመላክቷል፡፡ በተጨማሪም ከስራ ክፍሉ የብቃት ማረጋገጫ ስርተፊኬት ለተሰጣቸው 30 ተቋማት ተገቢውን የቢሮና የመጋዘን ኢንሰፔክሽን  በማድረግ ሰርተፊኬታቸውን የማደስ ስራ ይከናወናል እንዲሁም በዕፅዋትና የግብርና ምርቶችን ስራ ብቃት ማረጋገጫ

የወሰዱ 36 ለንግድ የሚሰሩ ድርጅቶች /ግለሰቦች በመስፈርቱ መሰረት እየሰሩ ሰለመሆናቸዉ ክትትልና ግምገማ ይደረጋል፡፡ 120 ለሚሆኑ በምርምር የቀረቡ ዕጩ የዕፅዋት ዝርያዎችን ግምገማ ይካሄዳል፡፡ እንዲሁም 78 ለሚሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎች ጥራትና ዉጤታማነታቸው ተረጋግጦ ይመዘገባሉ ይለቀቃሉ ተብሎ በዕቅዱ ላይ ተካቷል፡፡ በተጨማሪም

1,527,905 ኩ/ል የአገር ውስጥ ዘር በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱን የማረጋገጥ ስራ ይከናወናል፡፡ ሌላው 250 የሚሆን ከውጪ የገባ ዘር ናሙና ጥራቱ በላብራቶሪ እንዲፈተሽ ይደረጋል፡፡ 509,603 ኪሎግራም የሚሆን ከውጭ አገር የሚገባ ዘር  በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ ይረጋገጣል፡፡ ከዚህ ባለፈ 30 ለሚሆኑ ዘር ስራ ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡ በ2017 በጀት ዓመት ከተካተቱት እቅዶች አንዱ ደረጃውን የጠበቀ የእፀዋት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ አገልግሎት መስጠት ነው፡፡ በዚህም መሰረት አንድ (1) ማእከል የሆነ የላቦራቶሪ ኢንፎርሜሽን ማኔጅመንት ሲስተም ፕሮግራም (LIMS/IT-Program)) አገልግሎትን ይጀምራል፣ የእጽዋት ግብአት ምርት ጥራትና ደህንነት ምርመራ የሚሰሩ ተቋማትን በመለየት ዕውቅና የሚሰጥበት አሰራርን ይዘረጋል፡፡ በክልሎችና በፌደራል ደረጃ ባሉ የዘር ጥራት ምርመራ ላብራቶሪዎች በአጠቃላይ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ሰነድ ይዘጋጃል፣ ለስድስት (6) የላብራቶሪ አናሊስቶች የላቦራቶሪ የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፡፡ እንዲሁም ለአራት (4) ላብራቶሪዎች የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት የጥራትና ደህንነት ፍተሻ/ ምርመራ ስራ በሚሰሩ ቤተ-ሙከራዎች ላይ የኢንስፔክሽንና የኦዲት ስራ ማከናወን ሲሆን ሌላው ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ የእፅዋት ላቦራቶሪ የምርመራ መሳሪያዎች፣ የኬሚካል ግብአቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው የእፅዋት ላቦራቶሪ ቁሳቁሶች የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ የእፅዋት ላቦራቶሪ የምርመራ

ወደ ገፅ 8 ዞሯል

## ለኢትዮጵየ ግብርና ባለስልጣን አመራሮችና ሰራተኞች ቢሮን በካይዘን እሳቤ ማደራጀትን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጠ፡፡







የኢትዮጵየ ግብርና ባለስልጣን መካከለኛ አመራሮችና ሰራተኞች ቢሮን በካይዘን እሳቤ ማደራጀትን በተመለከተ በባለስልጣኑ መሰብሰቢያ አዳራሽ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጠ፡፡

ስልጠናውን በንግግር የከፈቱት የስራ አመራር ዋና ስራ አስፈፃሚ የሆኑት አቶ አበበ ገለታ ሲሆኑ እሳቸውም የዚህ ስልጠና ዋና ዓላማ በካይዘን ፅንሰ ሀሳብ እና በትግበራ አካሄዱ ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር፤ እንዲሁም የካይዘን ፕሮጀክት ትግበራ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የጋራ ሀሳብና አቅም እንዲኖር ለማገዝ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ በመቀጠልም የካይዘን ፅንሰ ሃሳብ፤ 5ቱ ውጤታማ የለውጥ መገንቢያ ምሰሶዎች፤የካይዘን የመጨረሻ ግቦች ጥሩ የስራ ባህል መገንባትና ተወዳዳሪነትን ማሳደግ እንደሆኑ፤ የካይዘን ቁልፍ መለኪያዎች ምርታማነት፤የአገልግሎት ጥራትና አካባቢያዊ ጉዳዮች እንደሆኑ እና በካይዘናዊ ስራ አመራር ፅንሰ ሃሳብ ዙሪያ ከካይዘን ልህቀት ማዕከል በመጡ ባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ማዕከሉ በባለስልጣን መ/ቤቱ ቀደም ብሎ ያደረገው ዳሰሳዊ ጥናት ሪፖርት ቀርቦ ሰፊ ውይይት ተደርጎበታል ፡፡

በመጨረሻም ከቤቱ በተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ላይ በአሰልጣኞች ተጨማሪ ማብራሪያ ከተሰጠ በኋላ ሰልጣኞች ቢሮአቸውን በካይዘን እሳቤ ለማደራጀት የጋራ መግባባት ላይ ተደርሶ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መድረኩ ተጠናቋል፡፡ ከገፅ 7 የዞረ

መሳሪያዎች፣ የኬሚካል ግብአቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው የእፅዋት ላቦራቶሪ ቁሳቁሶች የሚገቡባቸውን መስፈርቶች ማሟላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ የጉምሩክ ማስለቀቂያ ደብዳቤ ይሰጣል፡፡ የተዘረጋ የእጽዋት የላቦራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት ስርዓት ISTA-Accreditation and (ISO/IEC 17025) የምርመራ ሥነ-ዘዴ ትክክለኛነት (Test Method Verification/validation) ማረጋገጫ ተግባራትን ማከናወን፣ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ዓመታዊ ካሊብሬሽን ፣ ጥገና ማከናወን፣ የምርመራ ብቃት ማረጋገጫ (PT) በዘር ጥራት እና በምግብ ደህንነት ናሙናዎች ላይ ተሳትፎ ማሳደግ፣ የጥራት ማኔጅመንት ስርዓት ትግበራ የውስጥ ኦዲት ማከናወን፣ የላቦራቶሪ መረጃ ስርዓት ማዘመንና የመረጃ አቅርቦትና አጠቃቀም ማሻሻል (የላቦራቶሪ ምርመራ እና ተያያዥ ቴክኒካል ሥራዎች መረጃ ማደራጀትና ከላይ በተገለፁት ላይ በትኩረት እንደሚሰራ አስታውቋል ፡፡

### ምርጥና አስተማሪ አባባሎች

መልካም ሰዎች ልክ እንደ ጨረቃ ናቸው ዙሪያህ ሲጨልም ብርሃን ይሆኑልሃል

እውነትን በመከተልህ ምክንያት የምታጣው ውሸትንና ግብረ አበሮቹን ብቻ ነው

ከታሪክ የማይማሩ ሰዎች ስህተታቸውን ይደግማሉ

ትምህርት ለዕውቀት ያዘጋጃል እንጂ ዕውቀትን አይጨርስም ። ዕውቀትህን የምትይዝበትን ሥነ-ሥርዓት ግን ያሳይሃል ። አእምሮህን ለማረቅ ትምህርት ፣ ሰውነትህን ለመግዛት ትዕግስት ፣ ከማንም ጋር ለመኖር ሥነ-ሥርዓት ያስፈልግሃል ። ለህሊናህ እረፍት ግን እምነት ያሻሃል ። ተከታይ ለማበጀት ደግሞ ግልጽ መሆንና ታማኝነት ግድ ይልሃል ።




### አስገራሚ እውነታዎች! ▯▯

- በአሜሪካ እ.አ.አ በ1903 አ.ም ነው እነዚህ 2 ሰዎች ዊልያም ዌስት እና ዊልያም ዌስት ይባላሉ ምንም አይነት ዝምድና የላቸውም ሁለቱም በተመሳሳይ ጊዜ leavenworth ወደ ሚባል እስር ቤት በእኩል ጊዜ ይላካሉ በዚህም ጥበቃዎቹ ግራ ይጋባሉ በስተመጨረሻም የተረዱት አንድ ነገር ቢኖር ሁለት የተለያዩ ታሳሪዎች በተመሳሳይ ጊዜ በተመሳሳይ ስም ተመሳሳይ መልክ ኖሯቸው መምጣታቸውን ነው ። ታዲያ በእነዚ ሁለት ግለሰቦች የተነሳ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ Fingerprint (አሻራ) ሊፈጠር የቻለው ! ! !



👉 በሃገራችን ብዙ ጊዜ የሰርግ ሙዚቃ የምትሰሙት የሙሽሪትን ውበት ለመግለፅ " ችቦ አይሞላም ወገቧ" ይባላል ። ይህ ነገር ግን የማይመለከታቸው ኅሳዎች አሉ ፤ በማውሪታኒያ ሚስት ግዴታ ወፍራም መሆን አለባት እንደውም በጣም እንድትወደድ ዝሆን ብታክል አሪፍ ነው ፤ ምክንያቱም በነሱ አስተሳሰብ ወፍራም ሚስት የሃብት እና የብልጽግና ምልክት ተደርጋ ትወሰዳለች ። የዛ ሀገር ወንዶች ሀብታም ነኝ ማለት አይጠበቅባቸውም በቃ ግብዳ ሚስት አለኝ ካለ ሁሉም ይቀናበታል ። በማውሪታኒያ ቀጠን ያለች ሴት ልጅ ያላቸው ቤተሰቦች ቀደም ብለው ሙሽሪትን ለማደለብ በደላላም ሆነ በሌላ መንገድ የተለያዩ ማወፈሪያ መንገዶችን ይጠቀማሉ ።